# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 224821

ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- መኪያ ኢንተርፕራይዝ(ወ/ሮ መኪያ ማሚዬ ሲኪሳ) ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ሁሴን ናስር መሀመድ፡- ጠበቃ ሳሙኤል ከበረ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ቼክ ፈርሞ ለማዉጣት የሚያስችል የዉክልና ሥልጣን እና በቼክ ክርክር የሚቀርብ መከላከያ አይነት የሚመለከት ሆኖ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረቱት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካችና ተጠሪ የሳውዲ ጀርመን ሆስፒታል ኃ/የተ/የግ/ማኅበር ማኅበረተኞች እንደሆኑ፤ተጠሪ በዚህ ማኅበር ካላቸዉ 500 አክሲዮኖች (ድርሻ) ውስጥ 265 አክሲዮኖች በብር 30,000,000.00(ሰላሳ ሚሊዮን ብር) ለአመልካች መሸጣቸዉን፤ አክሲዮኖቹን በሽያጭ ማስተላለፋቸዉን የሚያሳዩ ቃለ-ጉባኤና ውል በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ዋና መስሪያ ቤት መመዝገባቸዉን፤ ተጠሪ አክሲዮኖቹን የገዙበትን ዋጋ ለመክፈል ቀኑ ወደፊት ተደርገዉ የተጻፉ ቼኮችን ፈርመዉ መስጠታቸዉን፤ አመልካች ከሰጡት አራት ቼኮች ውስጥ በቀን 29/10/2011 ዓ/ም(እ.ኤ.አ በቀን 06/07/2019ዓ/ም) በተፈረመው ቼክ ብር 5,000,000.00(አምስት ሚሊዮን ብር) መከፈላቸዉን፤ በቀሪ ሶስት ቼኮች ማለትም ብር 5,000,000.00(አምስት ሚሊዮን ብር) የተጻፈበትን ቁጥሩ C02219317 የሆነ በቀን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

20/02/2012 ዓ/ም የሚመነዘር ቼክ፣ ብር 10,000,000.00(አስር ሚሊዮን ብር) የተጻፈበትን ቁጥሩ C02219318 የሆነ በቀን 22/08/2012 ዓ/ም የሚመነዘር ቼክ፣ ብር 10,000,000.00(አስር ሚሊዮን ብር) የተጻፈበትን ቁጥሩ C02219319 የሆነ በቀን 21/02/2013 ዓ/ም የሚመነዘር ቼክ እንደሰጧቸዉ፤ ተጠሪ ቼኮቹን ለመመንዘር አሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ቀርሳ ዋና ቅርንጫፍ ስሄዱ የባንክ ሂሳቡ ቼኮቹ ተፈርመዉ ከመዉጣታቸዉ በፊት ሂሳቡ በፍርድ ቤት የታገደ ፣በቂ ስንቅ የሌለዉ እና በአመልካች በራሳቸዉ በቀን 17/07/2012ዓ/ም የታገደ መሆኑ ተገልጾ በባንኩ ማስረጃ እንደተሰጣቸዉ በመግለጽ አመልካች ቀሪ ብር25,000,000.00(ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) ቼኮቹንን ፈርመው ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ 9 % ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በአጭር ሥነ ሥርዓት ታይቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ክሱን መከላከል እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸዉ ያቀረቡትን ማስፈቀጃ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ መከላከያ እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸው ለክሱ በሰጡት መልስ ተጠሪ ያቀረባቸው ቼኮች ላይ ያለው ፊርማ የአመልካች አይደለም፡፡ ቼኮቹ በአመልካች ወይም ቼክ ለመፈረም ልዩ ዉክልና በተሰጠዉ ሰዉ የተፈረሙ አይደሉም፡፡ የተጠሪ ፊርማ ለጠበቃቸዉ በሰጡት ዉክልና ላይ የተመለከተዉ አይነት ነዉ፡፡አስፈላጊ ከሆነ አመልካች የባንክ ሂሳብ ለመክፈት በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ፣በኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አፍርካ ጎዳና ቅርንጫፍ የሰጡት የፊርማ ናሙና ቀርቦ ሊነጻጸር ይችላል፡፡ልዩነቱ ግልጽ ስለሆነ ጉዳዩ ወደ ፎንሲክ መሄድ ሳያስፈልግ በአይን እይታ መለየት የሚቻል ነዉ፡፡ስለሆነም ተጠሪ መብት አለኝ የሚሉ ከሆነ አግባብነት ባለዉ ሕግ ጥያቄያቸዉን ከማቅረብ በቀር ቼክን መሰረት አድርገዉ ክስ እንዲያቀርቡ የንግድ ሕጉ ቁጥር 712/2 አይፈቅድላቸዉም፡፡በመሆኑም የቀረበው ክስ ከበቂ ወጪና ኪሳራ ጋር ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 258092 ላይ ግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች እንዲሁም በራሱ ትእዛዝ ያስቀረበዉን ማስረጃ አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሮ በቀን 07/12/2013 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ለክሱ መሰረት የሆኑትን ሶስት ቼኮች ኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ ለመኪያ ኢንተርፕራይዝ ያሳተማቸዉ መሆኑ ክርክር አላስነሳም፡፡መኪያ ኢንተርፕራይዝ በኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ በሂሳብ ቁጥር 1000000641514 የሚንቀሳቀሰዉን ቼክ ፈራሚ ተብለዉ በባንኩ የሚታወቁት አቶ ካሚል አብዱልቃዲር መሆናቸዉን፤ይህንም የሚያደርጉት ወ/ሮ መኪያ ማሚዬ በቀን 12/10/1990ዓ/ም በሰጧቸዉ ዉክልና መሰረት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ መልኩ ወ/ሮ መኪያ ማሚዬ ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የሰጡት ዉክልና ይዘት እንደተመረመረዉ የዉክልናዉ ይዘት "…ማንኛዉንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በስሜ እንደእኔ ሆነዉ ለመግዛት፣ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ፣ ስም ለማዛወር፣ ገንዘብ ለመቀበል፣ ዉል ለመዋዋል፣ ለመፈረም፣ ከባንክ በስሜ ለመበደር፣ የባንክ ሂሳብ ማንኛዉንም ዓይነት ሂሳብ ለመክፈትና ለማንቀሳቀስ፣ለማዉጣት ለማስገባት፣…" የዉክልና ሥልጣን የሰጧቸዉ እንደሆነ ያሳያል፡፡ከዚህ የዉክልና ይዘት በተለይ "…የባንክ ሂሳብ ማንኛዉንም ዓይነት ሂሳብ ለመክፈትና ለማንቀሳቀስ፣ለማዉጣት ለማስገባት…" የሚለዉ ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የሰጡት ሥልጣን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2206/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት የልዩ ዉክልና ተከታታይና ተመሳሳይ ድርጊት እንደሆነ ያሳያል፡፡ ስለሆነም በክሱ የተጠቀሱት ቼኮች ልዩ ዉክልና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በተሰጣቸዉ በአቶ ካሚል አብዱልቃዲር አማካይነት ለተጠሪ ተፈርመዉ የተሰጡ ስለሆኑ ተጠሪ የንግድ ሕጉን አንቀጽ 854 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ያቀረቡት ክስ የሚነቀፍ አይደለም፡፡የቼክ ቁጥር C02219317 የሆነዉ ቼክ ለክፍያ በቀረበ ቀን የአመልካች ሂሳብ በቂ ስንቅ ስላልነበረዉ ብሎም ሂሳቡ በፍርድ ቤት በመታገዱ ክፍያ ሳይፈጽም መቅረቱን፣የቼክ ቁጥር C02219318 የሆነዉ ቼክ ለክፍያ በቀረበበት እለት ክፍያ መታገዱን እንዲሁም ቼክ ቁጥር C02219319 ለክፍያ በቀረበ ቀን አመልካች ሂሳብ ዉስጥ በቂ ስንቅ ባለመኖሩ፣ክፍያ በመታገዱ እና ሂሳቡ በመዘጋቱ ክፍያ ሳይፈጸም መቅረቱን ፍርድ ቤቱ በማስረጃ አረጋግጧል፡፡በዚህ መሰረት አንድ ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል የክፍያ ሰነድ ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 854 ስር የተደነገገ በመሆኑ አመልካች በወኪላቸዉ አማካኝነት ፈርመዉ በሰጡት ቼኮች ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ብር 25,000,000.00(ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) ቼኮቹ ለክፍያ ከሚቀርቡበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9 % ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ እና ክሱ ያስከተለባቸዉን ወጪዎች ለተጠሪ እንዲተኩላቸዉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ችሎቱ በመ/ቁጥር 214449 ላይ በቀን 30/06/2014 ዓ/ም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት በሰጠዉ ትዕዛዝ ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 04/08/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡-ለክሱ ምክንያት በሆኑት ቼኮች ላይ የተፈረመው ፊርማ የአመልካች አይደለም፡፡ ቼኩን ፈርመዋል የተባሉት ግለሰብ በአመልካች ስም ቼክ ፈርመው ለማውጣት የሚያስችል ልዩ ውክልና አልተሰጣቸውም፡፡ ልዩ ዉክልና የሚያስፈልጋዉ እነማን እንደሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2205/1 ስር በምሳሌነት ተዘርዝረዉ ይገኛሉ፡፡ከእነኚህ አንዱ የለዉጥ ግዴታ ዉል(በንግድ ሕጉ ሥያሜ የሃዋላ ወረቀት/bill of exchange) ነዉ፡፡ የሃዋላ ወረቀት እና ቼክ በንግድ ወረቀት/commercial instruments ዉስጥ ተካተዉ የሚገኙ ናቸዉ፡፡ስለዚህ ቼክ ቀረቤታ ያለዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2205/2 ስር ካለዉ የለዉጥ ግዴታ ዉል ጋር እንጂ የባንክ ሂሳብ ማንቀሳቀስ ከሚለዉ ጋር ስላልሆነ ቼክ ፈርሞ ለማዉጣት በዉክልና ዉስጥ ቼክ መፈረም የሚል በግልጽ የተመለከተ ልዩ ዉክልና ሊኖር ይገባል፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2205/2 እና በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827/ሠ ስር የተመለከተዉን ድንጋጌ በተሳሳተ መንገድ በመተርጎ የሰጠዉ ዉሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሐ) መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በክሱ ላይ የመፈረም ስልጣን በሌለው ሰው የተፈረመ ነው እያሉ ይህ መከራከሪያቸዉ ታልፎ የተወሰነበትን አግባብነት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2205/2 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 827/ሠ አንፃር ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 01/09/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡የመልሳቸዉም ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ድርሻ የማስተላለፍ ውል የነበረ መሆኑንና እዳ እንዳለባቸው በተደረገው ክርክር አምነዋል፡፡በመሰረቱ ቼኮቹን ፈርመዉ የሰጡት

በዉሉ መነሻ ነዉ፡፡ቼኮቹን የፈረሙት የአመልካች ባለቤት የሆኑት ግለሰብ እንደሆነ ተጠሪ ያቀረብኩትን መከራከሪያ አመልካች በስር ፍርድ ቤት አላስተባበሉም፡፡በዉክልና ሥልጣናቸዉም ማንኛዉንም የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ እንዲያንቀሳቅሱ የሚለዉ በቼክ ማንቀሳቀስን የሚያጠቃልል ነዉ፡፡ውክልናቸውም ግልፅ የሆነ ልዩ ውክልና ነው፡፡እንዲሁም ቼኩን የፈረሙት ግለሰብ ለባንክ የፊርማ ናሙና የሰጡ ናቸዉ፡፡ ቼክ ፈራሚው የአመልካች ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ መሆናቸውን በስር ፍርድ ቤት አስረድተናል፡፡ ሂሳቡም የንግድ ድርጅታቸዉ በመሆኑ ልዩ ዉክልና ባይኖራቸዉ እንኳን በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 34/1 መሰረት ድርጅቱን እስከመሩ ድረስ የሚተላለፉ ሰነዶችን ለመፈረም ሥልጣን እንዳላቸዉ እንደሚቆጠር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ቼኩን ለፈረሙት ግለሰብ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2206/1 መሰረት ልዩ ዉክልና ተሰጥቷቸዋል ሲል የሥር ፍርድ ቤት በደረሰበት ድምዳሜ የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ አመልካች ቼኮቹን የፈረሙት ግለሰብ ልዩ ዉክልና የላቸዉም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካችም የመልስ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም በአመልካች የቀረበዉ መከራከሪያ ዉድቅ ተደርጎ በክሱ ላይ የተጠቀሱትን ቼኮች ፈርመዉ ያወጡት ግለሰብ ቼኮቹ ላይ ለመፈረም የሚያስችል የዉክልና ሥልጣን አላቸዉ በሚል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍሉ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት ክሱ ላይ በተጠቀሱት ሶስት ቼኮች ላይ የተመለከተዉን ብር 25,000,000.00 ከሕጋዊ ወለድና ክሱ ካስከተለባቸዉ ወጪዎች ጋር ለማስከፈል ሲሆን አመልካች ቼኮቹን ለማዉጣት የሚያስችል ግንኙነት የለኝም በማለት አልተከራከሩም፡፡ሆኖም ቼኮቹ በአመልካች ወይም ቼክ ለመፈረም ልዩ ዉክልና በተሰጠዉ ሰዉ የተፈረሙ ስላልሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት ቼኮቹን አመልካች ራሳቸዉ የፈረሙት ባይሆንም በአመልካች ልዩ የዉክልና ሥልጣን በተሰጣቸዉ የአመልካች ተወካይ የተፈረሙ ስለሆኑ በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ አመልካች ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

በ1952 በወጣዉ የንግድ ሕጋችን በአንቀጽ 732፣827፣828 እና 854 ላይ እንደተመለከተዉ ቼክ የንግድ ወረቀት (Commercial instruments) ከሚባሉት ሰነዶች አንዱ ሆኖ በባንክ ተቀማጭ ሂሳብ ያለው ሰው ገንዘቡ ለራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሐተታ የሌለው ትእዛዝ ተሰጥቶበት እንደቀረበ የሚከፈል ገንዘብን ተክቶ ክፍያን የሚያቀላጥፍ የንግድ ወረቀት ወይም ተላላፊ ሰነድ ነው፡፡ እንዲሁም በቼክ ላይ የሚጻፉ አስፈላጊ መግለጫዎች ናቸዉ ተብለዉ በንግድ ሕግ አንቀጽ 827 ከፊደል ሀ እስከ ሠ ባሉት ንኡሳን አናቅጽ በተደነገገዉ መሰረት አንድ የቼክ ሰነድ ሀ) የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትእዛዝ፣ ለ) መክፈል የሚገባዉ ከፋይ ስም፣ ሐ) የሚከፈልበት ቦታ፣ መ) ቼኩ የወጣበት ቦታና ጊዜ እና ሠ) ቼኩን ያወጣዉ ሰዉ ፊርማ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡በዚሁ ሕግ አንቀጽ 828 ስር ባለዉ የመግቢያ ዐረፍተ ነገር ላይ

እንደተመለከተዉ ከእነዚህ መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ቼክ ክፍያ ተጠይቆበት ለባንክ በቀረበ ጊዜ ባንክ ክፍያ አልፈጽምም ማለት ይችላል፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል ሰነድ በመሆኑ በቼክ ገንዘብ ለመክፈል ቼክ አውጪ የሆነ ሰዉ በባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳቡ የተቀመጠ የቼኩን ዋጋ ሊከፍል የሚችል በቂ ገንዘብ (ስንቅ) እንዳለዉ እርግጠኛ መሆን ይኖርበታል(የንግድ ሕግ አንቀጽ 830/2 ይመለከቷል)፡፡ ይህንኑ በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ የቀረ ቼክ አውጪ በቼኩ ላይ የተጻፈውን ገንዘብ ለአምጪው እንዲከፍል በሕግ ይገደዳል፡፡ ቼክ አዉጪ በቼኩ ላይ የተጻፈዉን ገንዘብ ለአምጪዉ ለመክፈል አልገደድም ብሎ በመቃወም መከራከር የሚችለዉ አንድም ከአምጪዉ ወይም ሰነዱን ከያዘዉ ሰዉ ጋር ያለዉን ከግል ግንኙነት ጋር የተያያዘ መከላከያ በማንሳት (personal relations defences) ወይም ደግሞ በሰነዱ አጻጻፍ ፎርምና በሰነዱ ላይ በተጻፉት ቃሎች እንዲሁም ፊርማዉን በማስመሰል የተሰራ፣ ቼኩ ችሎታ ወይም የዉክልና ሥልጣን በሌለዉ ሰዉ ተፈርሞ ወጥቷል የሚሉ (real defences) እና ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች አልተሟሉም የሚሉ የመከላከያ መከራከሪያዎችን በማንሳት እንደሆነ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 እና 850 የተደነገገዉ ያሳያል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ መከላከያዎቹ በዋናነት በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ያለዉን የግል ግንኙነት(personal relations defences) ላይ እና የቼኩን ሰነድ ተከትለዉ የሚነሱ መከላከያዎች (real defences) ላይ የተሰወኑ መሆናቸዉን ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከትነዉ አመልካች በቼኮቹ ላይ የተገለጸዉን ገንዘብ ልከፍል አይገባም በማለት ሲከራከሩ ያነሱት የመከላከያ መከራከሪያ በቼኮቹ ላይ ያለዉ ፊርማ በራሳቸዉም ሆነ ልዩ ዉክልና በተሰጠዉ ሰዉ የተፈረመ እንዳልሆነ የሚገልጽ ነዉ፡፡ ይህም የአመልካች መከራከሪያ የቼኮቹን ሰነድ ይዘት (Content of Cheques) የሚመለከት እንደሆነ ስለሚያሳይ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717/2 እና 827/ሠ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ መከራከሪያ ነዉ፡፡በዚህ መሰረት አመልካች ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ተጠሪ ቼኮቹ ላይ የፈረሙት የቼክ ሂሳብ(ተንቀሳቃሽ ሂሳብ) የሚያንቀሳቅሱ እና በአመልካች የተወከሉ ግለሰብ ናቸዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ቼኮቹ ላይ የፈረሙት ግለሰብ ማንነት እና ያላቸዉን የዉክልና ሥልጣን ለማጣራት በግራ ቀኙ የቀረቡ ማስረጃዎችንና በራሱ ያስቀረባቸዉን ማስረጃዎች በመመርመር በቼኮቹ ክፍያ ለመፈጸም የታዘዘዉ በኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ ካለዉ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ላይ ሲሆን በዚህ ባንክ የተቀመጠዉ የፊርማ ናሙና የአመልካች ወኪል የሆኑት የአቶ ካሚል አብዱልቃዲር እንደሆነ ፣ቼክ የሚንቀሳቀስበትን የፊርማ ናሙናቸዉን ለባንኩ ሊሰጡ የቻሉትም ሆነ በአከራካሪዎቹ ቼኮቹ ላይ ሊፈርሙ የቻሉት አመልካች ወ/ሮ መኪያ ማሚዬ "…የባንክ ሂሳብ ማንኛዉንም ዓይነት ሂሳብ ለመክፈትና ለማንቀሳቀስ፣ ለማዉጣት ለማስገባት…" በቀን 12/10/1990ዓ/ም በሰጧቸዉ የዉክልና ሥልጣን እንደሆነ ከተጠቃሹ ባንክ በትእዛዝ ከአስቀረበዉ ማስረጃ አረጋግጧል፡፡በዚህ መሰረት በቼኮቹ ላይ የተፈረመዉ በአመልካች ሳይሆን በወኪላቸዉ አቶ ካሚል አብዱልቃዲር መሆኑ በሕግ ፍሬ ነገርን ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ የማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠዉ የሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት አከራካሪዎቹ ቼኮች ላይ የተፈረመዉ የአመልካች ወኪል ናቸዉ በተባሉት በአቶ ካሚል አብዱልቃዲር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤትም ሆነ በዚህ ችሎት ደረጃ በቀን 12/10/1990ዓ/ም ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር ተሰጠ የተባለዉን የዉክልና ሥልጣን አልሰጠሁም በማለት ክደዉ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡እንዲሁም ለክሱ መነሻ በሆኑ ቼኮች የታዘዘዉ ገንዘብ የሚከፈልበት የቼክ ሂሳብ ማንቀሳቀስ እንዲችሉ ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የወክልና ሥልጣን በተጠቀሰዉ ቀን አልሰጠሁም በማለት ክደዉ አልተከራከሩም፡፡የአመልካች ክርክር ይህ ለአቶ ካሚል አበዱልቃዲር የተሰጣቸዉ የዉክልና ሥልጣን ልዩ ዉክልና ባለመሆኑ ቼክ የንግድ ሰነድ በመሆኑ በቼክ ላይ መፈረም ይችላሉ የሚል ግልጽ ዉክልና ሳይሰጣቸዉ መፈረም ስለማይችሉ በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ለመክፈል አልገደድም የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪ ደግሞ አቶ ካሚል አብዱልቃዲር የአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ መሆናቸዉንና የተሰጣቸዉን የዉክልና ሥልጣን ይዘት መሰረት በማድረግ በቼኮቹ ላይ ለመፈረም የሚያስችል ሥልጣን አላቸዉ በሚል ተከራክረዋል፡፡አቶ ካሚል አብዱልቃዲር ቼኮቹ ላይ የፈረሙት በሥራ አስኪያጅነት ሥልጣናቸዉ መሆን አለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የክርክር ነጥብ ሆኖ ቀርቦ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ ከዚህ አኳያ ተጠሪ ያነሱትን ክርክር አልፈነዋል፡፡

ከዉክልና ሥልጣን ረገድ ለቀረበዉ ክርክር ዉሳኔ ለመስጠት በቼክ ላይ ለመፈረም ልዩ ዉክልና እንደሚያስፈልግ ሕግ የሚያስገድድ መሆን አለመሆኑንና ሕግ ያስገድዳል የሚባል ከሆነ አመልካች ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የሰጡት ዉክልና ልዩ የዉክልና ሥልጣን መሆን አለመሆኑን መመርመር ይጠይቃል፡፡የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የሰጡትን የዉክልና ሥልጣን ማስረጃ ይዘት በመመርመር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2206/1 ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የተሰጣቸዉ የዉክልና ሥልጣን ልዩ ዉክልና በመሆኑ በቼክ ላይ መፈረም ስለሚችሉ ቼኮቹ ጉድለት የለባቸዉም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827/ሠ ላይ እንደተደነገገዉ በአንድ ቼክ ላይ የቼክ አዉጪዉ ፊርማ መኖር እንዳለበት ደንግጓል፡፡እንዲሁም በዚሁ ሕግ አንቀጽ 717/2 ስር እንደተመለከተዉ የዉክልና ሥልጣን በሌለዉ ሰዉ ቼኩ ላይ ስለተፈረመ ለመክፈል አልገደድም የሚል መከላከያ ሊቀርብ እንደሚችል የተደነገገ ቢሆንም በቼክ ላይ መፈረም የሚችለዉ ሰዉ ልዩ ዉክልና የተሰጠዉ ሰዉ ብቻ ነዉ በሚል በግልጽ በንግድ ሕጉ አልተደነገገም፡፡ የንግድ ሕጉ ስለዚህ ጉዳይ ዝም ካለ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለወኪልነት የተደነገገዉን መመልከት ያስፈልጋል፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2205/2 ስር "…የለዉጥ ግዴታ ዉል ለመፈረም/to sign bills of exchange…" ልዩ ዉክልና እንደሚያስፈልግ ደንግጓል፡፡ በዚህ መልኩ *የለዉጥ ግዴታ ዉል* ተብሎ የተገለጸዉ bills of exchange በንግድ ሕጉ አንቀጽ 732/2፣ 735 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የሐዋላ ወረቀት ተብሎ የተገለጸዉ ሲሆን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 732/2 ስር በተሰጠዉ ትርጓሜ መሰረት ከቼክ ጋር ከንግድ ወረቀቶች አንደ አንዱ የተቆጠረ ነዉ፡፡እንዲሁም በቼክ ላይ መፈረም በዉክልና ሥልጣን እንደሚከናወን የአስተዳደር ሥራ የሚቆጠር ተግባር አለመሆኑን የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2204 ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2205/2 ስር በሐዋላ ወረቀት ላይ ለመፈረም ልዩ የዉክልና ሥልጣን ያስፈልጋል ተብሎ የተደነገገዉ

የሐዋላ ወረቀት ከንግድ ወረቀቶች አንዱ በመሆኑ የንግድ ወረቀት የሆነዉን ቼክ ለመፈረምም ልዩ የዉክልና ሥልጣን ያስፈልጋል ብለናል፡፡በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የሰጡት የዉክልና ሥልጣን ልዩ ዉክል ነዉ ብሎ ፍርድ ሲሰጥ በቼክ ላይ ለመፈረም ልዩ ዉክልና እንደሚያስፈልግ ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ የፍርዱ ይዘት ስለሚያሳይ ከዚህ አኳያ የደረሰበት ድምዳሜ የሕግ ድጋፍ ያለዉ ነዉ፡፡

እንዲሁም የቼክ ወይም ተንቀሳቃሽ ሂሳብ (Cheque/Current Account) ስሙ እንደሚያመላክተዉ በቼክ የሚንቀሳቀስ ነዉ፡፡ብሔራዊ ባንክ በአወጣዉ መመሪያ ቁጥር SBB/31/2002 አንቀጽ 1.2 እና በመመሪያ ቁጥር SBB/63/216 አንቀጽ 2.3 ስር የተሰጠዉ ትርጓሜም ይህንኑ ያሳያል፡፡አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2205/2 ስር እንደተደነገገዉ አቶ ካሚል አብዱልቃዲር *በቼክ ላይ እንዲፈርሙ* በሚል በግልጽ አስፍረዉ ዉክልና አለመስጠታቸዉ አከራካሪ አይደለም፡፡ሆኖም የስር ፍርድ ቤት በፍርድ ሀተታዉ ላይ በግልጽ እንዳሰፈረዉ አመልካች ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር በሰጡት የዉክልና መስጫ ሰነድ ላይ አቶ ካሚል አብዱልቃዲር "…የባንክ ሂሳብ ማንኛዉንም ዓይነት ሂሳብ ለመክፈትና ለማንቀሳቀስ፣ለማዉጣት ለማስገባት…" እንዲችሉ አመልካች የዉክልና ሥልጣን ሰጥተዋቸዋል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2206/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት ልዩ ዉክልና በላዩ ተዘርዝረዉ የተመለከቱትን ጉዳዮች ለመስራት ብቻ ሥልጣን የሚሰጥ ሳይሆን የእነዚሁ ተከታታይና ተመሳሳይ የሆኑ ጉዳዮችን ለማከናወን ጭምር ሥልጣን የሚሰጥ ነዉ፡፡ አመልካች ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር ማንኛዉንም የባንክ ሂሳብ ለመክፈትና ለማንቀሳቀስ ሥልጣን እንደሰጧቸዉ እስከተረጋገጠ ድረስ አቶ ካሚል አብዱልቃዲር በቼክ የሚንቀሳቀስ የባንክ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ፡፡የቼክ ሂሳብ ማንቀሳቀስ የሚቻለዉ ከላይ በተጠቀሰዉ መመሪያ ቁጥር SBB/63/216 አንቀጽ 2.3 ትርጓሜ መሰረት ቼክ በማዉጣት ነዉ፡፡ቼክ ማዉጣት ደግሞ ቼክ ላይ መፈረምን የሚጠይቅ ነዉ፡፡በዚህ መልኩ በቼክ ላይ የመፈረም ተግባር አመልካች ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የሰጧቸዉ ማንኛዉንም የባንክ ሂሳብ የመክፈትና የማንቀሳቀስ ልዩ የዉክልና ሥልጣን ተከታይ ነዉ ብለናል፡፡

በመሆኑም አመልካች ለአቶ ካሚል አብዱልቃዲር የሰጧቸዉ ማንኛዉንም የባንክ ሂሳብ የመክፈትና የማንቀሳቀስ የዉክልና ሥልጣን የዚህ ተከታይ የሆነዉን በቼክ ላይ የመፈረም ሥልጣን የሚሰጣቸዉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2206/1 ስር የተደነገገዉን በመጥቀስ የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ ተገቢዉን የሕግ አተረጓጎምና አተገባበር የተከተለና የዉክልና ሥልጣን ማስረጃዉ ይዘት ድጋፍ ያለዉ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 258092 ላይ በቀን 07/12/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 214449 ላይ በቀን 30/06/2014 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. የፍርድ አፈጻጸም እንዲታገድ የተሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም